አፍሪካ ቲቪ

2

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም

6

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- 7) ሀይድና ውስጥ ላሉ ቁርአን መንካትን በተመለከተ
- ከነቢዩ ሰለላሁ ጀናባዐለይሂ ወሰለም እንደተወራው

عن أبي بكر بن محمد بن عمرو بن حزم عن أبيه عن جده أن النبي صلى الله عليه وسلم كتب إلى أهل اليمن كتاباً وكان فيه " لا يمس القرآن إلا طاهر". [ورواه مالك مرسلاً بلفظه].

- (ንፁህ ካልሆነ (ሰው) በስተቀር ቁርአንን አይንካው።)
- የሚለውን ሙርሰል ሀዲስ ምሁራን ተቀብለውታል።
- ይህንንም በማስመልከት ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ቀጣዩን አስተላልፈዋል።

{ ኢማሙ አህመድ እንዳሉት ነቢዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ቁርአንን ንፁህ ያልሆነ አይንካው የሚለውን ለየመን ህዝቦች በፃፉት ደብዳቤ ላይ ማስፈራቸው ጥርጥር የለበትም።

- እንዲሁም ይህ ቃል የሰልማን አልፋሪሲ እና የአብደላህ ኢብኑ ዑመር ብሎም የሌሎች ሰሃቦች ጭምር ነው። ከሰሃቦች መካከልም ይህንን የሚቃረን አይታወቅም። }
- ሲሉ ቁርአን በአካል ቀጥታ መነካት እንደሌለበት አስረድተዋል።



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

አፍሪካ አካዳሚ

- 8) መስጂድ ውስጥ ገብቶ መቀመጥ

ሌላው ሀይድ ላይ ያለች እንስት የምትከለከለው ጉዳይ በመስጅድ ውስጥ መቀመጥ ነው። አንዲት ሀይድ ላይ ያለች እንስት የዒድ መስገጃ ቦታ ላይ ጨምሮ መስጂድ ውስጥ መቀመጥ ትከለከላለች። ኡሙ አጢያህ ረዲየላሁ ዐንሀ ባወራችን ሀዲስ ነቢዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም

(يخرج العواتق وذوات الخدور والحيض) وفيه : (يعتزل الحيض المصلى) متفق عليه

(ልጃ ገረዶች፣ ለጋብቻ የደረሱ ሴቶችና ሀይድ ላይ ያሉትም ጭምር ወደ ዒድ ሰላት ስፍራ ይወጣሉ (ይሄዳሉ)...» በሚለው ሀዲሳቸው ላይ «ሀይድ ላይ ያሉት ግን ከሙስሊሞችን የመስገጃ ቦታ ገለል ይላሉ።» የሚል ዘገባ በቡኻሪና ሙስሊም ድርሳን ስላለ



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

አፍሪካ አካዳሚ

- ለዒድ ሰላት እንኳን ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር እንዲጓዙ እያዘዟቸው የመስገጃ ቦታዋን ግን እንዲርቁ አስጠንቅቀዋልና ሀይድ ላይ እስካሉ ድረስ መስጅድ ውስጥ መቀመጥ አይፈቀድላቸውም። ይህም የአራቱም መዝሀብ አቋም ነው።
- ለቀላል ጉዳዮች ግን እጅ ሰንዝሮ እቃ እንደመቀበልና ማቀበል እንዲሁም ደሙ አይንጠባጠብም ብላ ከተማመነች ለአስፈላጊ ጉዳይ በመስጂዱ ውስጥ አቋርጦ እንደማለፍና የመሳሰሉት ለችግር እስከሆነ ደረስ የታገዱ አይደለም።

አፍሪካ አካዳሚ

- የወር አበባ ላይ የነበረች ሴት ከወር አባባ መጽዳቷን (ንፁህ) መሆንዋን በምን ታውቃለች?
- 1) ደሙ በማቆም እና በመድረቁ
- 2) (አል ቀሰቱል ቤይዳዕ) ነጭ የሆነ ፈሳሽ ምልክት ማየት
- 3) ብልት ከደም ሙሉ በሙሉ ንጹህ መሆን
- 4) ደፍረስ ያለ ወደ ዳለቻ መልክ የሄደ የደም ዓይነት እና ከወር አበባ ደም ጋር ያልተያያዘ በመሆን እና ወር አበባው ሲቆም የሚታይ፤
- በየወሩ የታወቁና የተለመዱ የወር አበባ ቀናት ያላትና
 ከዚያ ታዋቂው ቀንበፊት የቆመላት ሴት ንፁህ መሆኗን
ነው ሸሪዓው የሚያጸድቀው፡፡

2

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ

ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

አፍሪካ አካዳሚ

| ጉዳዩ | ብይኑ |
|---|---|
| ደም ከጊዜው ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ቢመጣባት | የወር አበባ ባህሪ ያለው ከሆነ በየትኛውም ሰዓት ቢሆን በመካከል ያሉት የንጽህና ቀናት ከአስራ ሶስት ቀን ካላነሰ የወር አበባ ነው። ይህ ካልሆነ ግን የበሽታ ደም ነው። |
| ከተለመደው የወር አበባ ዘመኑን ያለፈባት | ከአስራ አምስት ያልበለጠ ከሆነ የወር አበባ ነው። |
| ለብዙ ጊዜ ለወርና ከዚያም በላይ ደም የፈሰሳት ሴት | አራት ባህሪያት አሏት :-<br>1) የወር አበባዋን መምጫ ዘመንና ቀናት የምታውቅ የወር አበባን ደም ከሌለው መለየት የቻለች በቁጥሩና በሰዓቱ መሰረት ነው የምትጓዝው<br>2) የወር አበባዋን ቀናትና ዘመን የምታውቅ የወር አበባዋም ደም አንድ ዓይነት ባህሪ ያለው ከሆነ የምታውቀውን ዘመንና ቁጥር ታሳልፍ።<br>3) የወር አበባዋን መምጫ ዘመን የምታውቅ ነገር ግን የወር አበባ ቀናቷን የማታውቅ ከሆነ ሴቶች በብዛት የሚያሳልፉትን ስድስት ወይም ሰባት ቀናትን ታሳልፍ።<br>4) የወር አበባዋን መምጫ ዘመን አታውቅም ቁጥሩን ታውቃለች የጨረቃው ወር በተወለደ በመጀመሪያው ላይ ካሉት ቀናቶች ታስበው። |

2

አፍሪካ አካዳሚ

- **ማሳሰቢያዎች፡-**
- ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ከወር አበባና ከወሊድ ደም ስትፀዳ የዕለቱን ዙህርና ዐስር መስገድ ግዴታዋ ነው፡፡ ጎህ (ፈጅር) ከመውጣቱ በፊትም ብትፀዳ የዕለቱን መግሪብና ዒሻእዕን መስገድ ትገደዳለች፡፡
- ኢስቲሃዳ (ከወሊድም ሆነ ከሀይድ ደም ያልሆነ የበሽታ ደም ያለባት ሴት) ሶላት መስገድ ግዴታ ያለባት ሲሆን ንምየሶኡጁይላቱ ዉዱእ የማድረግ ግዴታ አለባት፡፡

2

አፍሪካ አካዳሚ

- **ወልዳ ደም ያላየች ሴት ብይን**

የወለደች ሴት ያላትን ውሳኔ አታገኝም፤ ትጥበትም የለባትም ፆሟም አይበላሽም፡፡

- **የመውለድ ምልክት ያየች ሴት**

የምታየው ደምም ይሁን ፈሣሽ ከመውለዷ በፊት ከህመም ጋር ከሆነ የወሊድ ደም ተብሎ አይጠራም፡፡ ይህ ከበሽታ የሆነ ደም ነውና፡፡

- **በመውለድ ላይ እያለች የሚፈሳት ደም**

ይህ የወሊድ ደም ነው፡፡ ልጁ ወጥቶም ይሁን ሳይወጣ ወይም በከፊል ቢወጣ በዚሁ ሰዓት ያለፋትን ሶላት ቀዷ ማውጣት አትገደድም፡፡

- **የወሊድ ቀናት መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ነው?**

ፅንሱ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ወደ ውጭ ከወጣበት ጀምሮ ነው፡፡

- **አነስተኛ የወሊድ ደም የሚቆይበት ቀን ስንት ነው?**

ለአነስተኛው መጠን የሌለው ሲሆን እንደወለደች ወዲያውኑ ደሟ ቢቆም ታጥባ መስገድ ይኖረባታል፡፡ የግድ አርባ ቀናትን መሙላት መጠበቅ የለባትም፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

አፍሪካ አካዳሚ

•ብይኑ

- **ከፍተኛው የወሊድ ደም ቆይታ ጊዜ ስንት ነው?**

አርባ ቀን ነው:: ከዚህ ከጨመረ ግን የበሽታ ደም ነው:: ከወር አበባ ደም ዘመኗ ጋር ካልተገናኘ በስተቀር ታጥባ መስገድ አለባት::

- **መንታ ወይም ከዚያ በላይ የወለደች ሴት**

የወሊድ ቀናት መቁጠር የምትጀምረው ከመቼ ነው?
የመጀመሪያው ፅንስ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ከወጣበት ጀምሮ ነው::

- **ከውርጃ በኋላ ያለ ደም**

ውርጃው የተከሰተው ከሰማኒያ ቀን ወይም ከዚያ ያነሰ ከሆነ የበሽታ ደም ነው:: ከዘጠና በላይ ከሆነ ደግሞ የወሊድ ደም ነው:: በሰማኒያና በዘጠና መካከል ያለው ደግሞ አፈጣጠሩ ታይቶ የሰው ቅርፅ ከያዘ የወሊድ ደም ይባላል:: ከሌለው ግን የበሽታ ደም ይባላል::

**•ከአርባ በፊት ፅድታ ከዚያም ከአርባ በፊት ደሙ ቢመለስባት**

በአርባ ቀን ውስጥ በምታየው ንፅህና ታጥባ መስገድ አለባት:: በዚሁ ውስጥ ከተመለሰባት ደግሞ የወሊድ ደም ይባላል:: እንዲሁ እያለ ደሙ እስኪቆምና አርባው ቀን እስኪሞላ ድረስ ይቀጥላል::

2

አፍሪካ አካዳሚ

•ብይኑ

• ወልዳ ደም ያላየች ሴት ብይን

የወለደች ሴት ያላትን ውሳኔ አታገኝም፤ ትጥበትም የለባትም ፆሟም አይበላሽም፡፡

• የመውለድ ምልክት ያየች ሴት

የምታየው ደምም ይሁን ፈሣሽ ከመውለዷ በፊት ከህመም ጋር ከሆነ የወሊድ ደም ተብሎ አይጠራም፡፡ ይህ ከበሽታ የሆነ ደም ነውና፡፡

• በመውለድ ላይ እያለች የሚፈሳት ደም

ይህ የወሊድ ደም ነው፡፡ ልጁ ወጥቶም ይሁን ሳይወጣ ወይም በከፊል ቢወጣ በዚሁ ሰዓት ያለፋትን ሶላት ቀዷ ማውጣት አትገደድም፡፡

• የወሊድ ቀናት መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ነው?

ፅንሱ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ወደ ውጭ ከወጣበት ጀምሮ ነው፡፡

• አነስተኛ የወሊድ ደም የሚቆይበት ቀን ስንት ነው?

ለአነስተኛው መጠን የሌለው ሲሆን እንደወለደች ወዲያውኑ ደሟ ቢቆም ታጥባ መስገድ ይኖረባታል፡፡ የግድ አርባ ቀናትን መሙላት መጠበቅ የለባትም፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

አፍሪካ አካዳሚ

•መንታ ወይም ከዚያ በላይ የወለደች ሴት የወሊድ ቀናት መቁጠር የምትጀምረው ከመቼ ነው?
የመጀመሪያው ፅንስ ሙሉ በሙሉ ከእናቱ ሆድ ከወጣበት ጀምሮ ነው፡፡

• ከውርጃ በኋላ ያለ ደም
ውርጃው የተከሰተው ከሰማኒያ ቀን ወይም ከዚያ ያነሰ ከሆነ የበሽታ ደም ነው፡፡ ከዘጠና በላይ ከሆነ ደግሞ የወሊድ ደም ነው፡፡ በሰማኒያና በዘጠና መካከል ያለው ደግሞ አፈጣጠሩ ታይቶ የሰው ቅርፅ ከያዘ የወሊድ ደም ይባላል፡፡ ከሌለው ግን የበሽታ ደም ይባላል፡፡

•ከአርባ በፊት ፀድታ ከዚያም ከአርባ በፊት ደሙ ቢመለስባት
በአርባ ቀን ውስጥ በምታየው ንፅህና ታጥባ መስገድ አለባት፡፡ በዚሁ ውስጥ ከተመለሰባት ደግሞ የወሊድ ደም ይባላል፡፡ እንዲሁ እያለ ደሙ እስኪቆምና አርባው ቀን እስኪሞላ ድረስ ይቀጥላል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com